# ገድለ ቅዱሳን ማንበብ

ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ለማሳደግ፣ ለእርሱና ለመንግሥቱ ያለንንም ፍቅር ከከፍተኛ ደረጃ ላይ ለማድረስ በጸጋው የምንጠቀምበት ሌላው መንፈሳዊ መንገድ የቅዱሳንን ሕይወት የሚያሳዩንን፣ የገድላቸውን መጻሕፍት ማንበብ ነው::

ገድለ ቅዱሳን መንፈሳዊ መመሪያዎችን በተግባራዊ መንገዳቸው ያቀርብልናል:: ከእግዚአብሔር ሕግጋት አብዛኛዎቹ በቃል ደረጃ ብቻ የተቀመጡ የሚመስለው ቢኖር እንኳን የቅዱሳንን ገድል ሲያነብ ትእዛዛቱ ሁሉ በዕለት ከዕለት ተግባራቸው፣ በሕይወታቸው ተፈጽመው ለአርአያነት ቀርበው ያገኛቸዋል::

እነዚህ መጻሕፍት ለቃል ብቻ የተሠጠ ሕግ እንደሌለና ሁሉም ያማሩ የተወደዱ እና በተግባር ሊውሉ የሚችሉ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ:: ብዙ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች «እነዚህን ትእዛዛት ማን ሊፈጽማቸው ይችላል?» የሚል የመገረም ጥያቄ ያነሳሉ:: እውነት ቀኝ ጉንጭን በጥፊ ለሚመታ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙሮ መስጠት ይቻላል? (ማቴ 5:39)፣ ሳያቋርጡ ልብንም ሳይከፍሉ መጸለይስ ሁሌ የሚቻል ነገር ነው? (ሉቃ 18:1፤ 1ተሰ 5:17)፣ ሰው ያለውን ሁሉ ለድሃ ሰጥቶስ ምን ይሆናል? (ማቴ 19:21) እነዚህን ሁሉ እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ግን በቅዱሳን ሕይወት ውስጥ ተመልሰው የምታገኛቸው ስለሆነ ገድላቸውን አንብብ::

ጌታም እነዚህ ቅዱሳን ለእኛ ሥነ ምግባራት ሁሉ አርአያና ምሳሌ እንዲሆኑን ይፈቅዳል:: በእውነት እነዚህ ቅዱሳን ከሥጋዊ ሕይወት፣ ከቁስ አካላዊነት ተለይተው የተጠሩበት ጥሪ ድንቅ ነው:: በእግዚአብሔር መንፈስ መኖር ስለቻሉና፣ በማናቸውም የጠላት ፍላጻዎች ላይ ፍጹም ድልን ስለተቀዳጁ በእውነት ምድራውያን መላእክት ናቸው:: ያለመጠራጠር የሰው ልጅ መጀመሪያ የተፈጠ



www.ethiopianorthodox.org

ረበትን የእግዚአብሔር አርአያና አምሳል መልሰው እንደታዩ መናገርም ይቻላል:: ለእኛም ሕይወታቸው በመንፈሳዊ መንገዳችን ላይ ያለጥርጥርና ፍርሃት መጓዝ እንድንችል ጽናትን ይሠጠናል:: ገድላቸውንም በምናነብበት ጊዜ «እነርሱን የረዳ አምላክ እኛንም ይረዳናል» ብለን በእርግጠኝነት እናምናለን::

የቅድስና ሕይወት ለፈለገውና ለመረጠው ሁሉ ይቻላል:: አሁን ካለንበት ደረጃ ከፍ ብለን የእግዚአብሔር ጸጋ በየልባችን እንዲሠራ እግዚአብሔር ፈቃዱ ነው:: የእግዚአብሔር መንፈስ ነፍስን ወደእግዚአብሔር በመምራት፣ ልዩ ሀብቶችን በመስጠትና በረድኤት ከክርስቲያኖች ጋር ይሠራል:: ቅዱሳን የሠሩት የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣቸው የሠራውን ነው:: ታሪካቸውን ስታስብ በሕይወታቸው ውስጥ እግዚአብሔር እንዴት እንደሠራና በእነርሱ እንደተመሠገነ አስተውለሃል?

የእነዚህ ሁሉ የጀግንነት ሥራዎቻቸው ምክንያትስ ገብቶሃል? በሚሠሩት ሥራ ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ጠንካራ ሕብረት እንደነበራቸው አትረዳም? (2 ቆሮ13:14)::

የቅዱሳን ሕይወት በዘመናት ውስጥ ትውልድ ላይ ጥልቅ አዎንታዊ ተጽዕኖ ነበረው:: በቅዱስ አትናቴዎስ የተጻፈው የቅዱስ እንጦንስ ታሪክም በሮም ሕዝብ ላይ እጅግ የሚያስገርም ለውጥ ያመጣና ለገዳማዊ ሕይወት መስፋፋት ትልቅ ምክንያት የሆነ ነበር:: ቀድሞ ፈላስፋ የነበረው አውግስጢኖስም ይህንኑ ታሪክ ሲያነብ ነው ከልብ ተነክቶበት በንስሓ ለመመለስ የበቃው:: በሲሐት በረኃ ይኖሩ የነበሩ መነኮሳትም ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው አርአያ የሆናቸው ከዓለም ተለይተው በበረሃ ይኖሩ የነበሩ አባቶች ሕይወት ነበር:: በእነዚህ ምድራውያን መላእክት ቅዱሳን አባቶች ሕይወት ተስበው እነሱን ለማየት ከሩቅ አገር፣ ረጅም ርቀት አቋርጠው መጡ:: መንፈሳዊ በረከት የሚያገኙበትን ምክራቸውን ሰሙ:: ብዙዎቹም ምግባር ትሩፋትን ካዩትና ከሰሙት በልቡናቸው ቀርጸው ማቆየት ቻሉ:: ይህም እስከአሁን ድረስ ለእኛ ከቅዱሳን ሕይወት መማር የምንችልበት ቅርሳችን ሆነ::



ቅዱሳን የራሳቸውን ገድል አልጻፉም:: ይሁን እንጂ በሌሎች አበው የተጻፈላቸው መጽሐፍ ዛሬ ለመንፈሳዊ ሕይወት ከሚያስፈልጉ ዋና ዋና ነገሮች አንዱ ነው:: ይህም አብረዋቸው በነበሩ አባቶች ተጽፎና ተነቦ ለቀጣዩ ትውልድ የተላለፈ ሕያው ታሪክ ነው:: ነቢያትና ሐዋርያትም በመንፈስ እግዚአብሔር ተነሳስተው ሲጽፉልንና ለእኛ ሲያደርሱን እራሳቸውን በስም ጠቅሰው ሳይሆን አብዛኛዎቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚገኙት ጽሑፎቻቸው ኋላ በስማቸው የተሰየመ ነው:: መጻሕፍቱም እግዚአብሔር በእነርሱ አማካይነት ያስተላለፈውን መልእክትና ድንቅ ሥራውን የራሳቸውንም የቅድስና ሕይወት በግልፅ ያሳዩናል::

ቤተክርስቲያናችን ለክብረ ቅዱሳን ታላቅ ሥፍራ ትሠጣለች:: ለክርስቲያኖች መጽናኛ እና የጥንካሬ ምንጭ እንዲሆን ገድላቸው በመጽሐፈ ስንክሳር ተመዝግቦ ይገኛል:: በጸሎተ ቅዳሴም ላይ ተደጋግሞ ይነሳል:: በተወለዱበት፣ ሰማዕትነትን በተቀበሉበትና እግዚአብሔር በእነርሱ አድሮ ታላላቅ ድንቅ ሥራዎችን ባደረገባቸው ዕለታት ቤተክርስቲያን አምላካቸውን ለማመስገን ስሙን ለማወደስ በስማቸው ታላላቅ መንፈሳዊ በዓላትን ታደርጋለች:: ዋናው ዓላማ በክርስቲያኖች ውስጥ «ከእግዚአብሔር ጋር ሁሉም ይቻላል» የሚለውን መርሀ ለማስረጽ ነው:: «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፣ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል»
(ዮሐ. 15:5)::

በየዕለቱ ሥራቸውን እንድናስታውስና ሕይወታቸው የመንፈስ ምግብ እንዲሆነን ስዕሎቻቸው በቤተክርስቲያን ውስጥ በፊታቸው ከሚበራ መብራት ጋር ይቀመጣል:: ይህ ደግሞ ለምእመኑ በተቀደሰ ተግባራቸው ሕሊናው እንዲመሠጥ ለበጎ ሥራ እንዲነሳሳ ምክንያት ይሆናል:: ማር ይስሐቅ ስለዚህ ነገር የሚነግርህ እጅግ ያማረ አገላለጽ አለው:: «አዲስ ችግኝ በውሃ ሕይወት የሚያገኘውን ያህል ገድለ ቅዱሳንም ለክርስቲያን ሕይወት የሚሠጥ ጣፋጭ ምግብ ነው::»



www.ethiopianorthodox.org

በእርግጥም ማንም ያለእርሱ ምንም መሥራት የማይችልበት መንፈሳዊ ምግብ ነው። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያደርሰውን መንገድ እንድናገኝ የሚመራን፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ጠለቅ ብለን እንድናስብ የሚያደርገንም ነው። ከዚህም በላይ የሥነ ምግባር ሰዎች መሆንን እንድንመርጥና፣ እነዚህን የእግዚአብሔር ሰዎች እንደ አባትና እናት አማላጆቻችን እንድንቀበላቸው የሚያደርግም ነው። ከቅዱሳኑ ጋር ያለንን ግንኙነት ለማጠናከር እንድንነሳሳ፣ ልክ እንደ እኛ በምድር አብረውን ያሉ እየመሰለን ከእነርሱ ጋር እንድንነጋገር እንድንጠራቸው የሚያስችል እግዚአብሔርን የማመስገኛ መንገድ ነው።

ለቅድስና ሕይወታቸውና ለእነርሱ ካለን ፍቅር የተነሳ አንዳንዴ ራሳችንን በስማቸው እንሰይማለን። ዛሬ እግዚአብሔር የተመሠገነ ይሁንና ብዙ ክርስቲያኖች በቅዱሳን ስም ይጠራሉ። በፍቅራቸውና በሥነ ምግባራቸው ተስበው እንዲያድጉ ለልጆቻችንም መጠሪያ ብናደርግላቸው ጠቀሜታው የጎላ ነው። ይህም ሁሉ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ የገለጸውን ድንቅ ሥራ ለማድነቅና ለእኛም ይደረግልናል በሚል ተስፋ የምናደርገው ነው። ለቅድስና ሕይወት ያለንን ታላቅ ክብር ለመግለፅ እና በቅዱሳን ስም ላይ ያለውን የእግዚአብሔር በረከት በማመን በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት መነኮሳት ምንኩስናን ሲቀበሉ አብረው የሚቀበሉት የእነዚህን ቅዱሳን አባቶች ስም ነው።

እኛስ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን እድገት ከቅዱሳን ያገኘነው ምንድን ነው?

1. አርአያነት

«የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ። የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው» (ዕብ 13:7)። ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው በፊታችን የተዘረጋ ሠፊ ፕሮግራም አለ። ማንም ለመያዝ ለፈለገው የትኛውም መልካም ሥነ ምግባር፣ የፈለገውን ወደሚያገኝበት የሚመሩትና በተግባር እያሳዩ፣እንደመልካም እጣን በቅድስና መዓዛ እየሳቡ የሚያደርሱት



ብዙ ቅድሳንን በፊቱ ያገኛል። በዘመንህ፣ በችሎታህ ሁሉ ክርስቶስን የመሠሉትን ቅዱሳን ምሳሌ አድርግ (1 ቆሮ 11:1)።

ለምሳሌ የሰማዕትነት ሕይወት ለእኛ እንደዚህ በቀላሉ የምናገኘው ላይሆን ይችላል። ይሁን እንጂ በእምነታቸው ጥንካሬ በትዕግስታቸው፣ በጽናታቸው፣ ለዘላዓለማዊ ሕይወት በነበራቸው ዝግጁነት፣ ዓለምንና ንብረቱን በመጥላታቸው ስማዕታትን እየተከተልን መጓዝ እንችላለን።

እንደ ቅዱስ አባታችን አባ ተክለሃይማኖት፣ ቅዱስ ገብረመንፈስ ቅዱስ እንደ ቅዱስ መቃርዮስ ዘእስክንድርያ ባለማቋረጥ መጸለይ ያቅተን ይሆናል። ቢሆንም ቢያንስ ለጸሎት ያለን ፍቅር እንዲጨምርና ያለንበት ደረጃ በሚፈቅድልን መጠን እየጸለይን ለመቀጠል እንድንናፍቅ ያደርጉናል። በበረሃ የነበሩት ቅዱሳን የሕይወት መንገዳቸው በዓለም ካለነው ከእኛ የአኗኗር ዘይቤ እጅግ የተለየ መሆኑን ማወቅ አለብህ። ስለዚህ ሕይወትህን ለእነርሱ እስከመዳረግ ድረስ በመጾም እነርሱን ለመምሠል መሞከር የለብህም። ቅዱሳኑ እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ ብዙ ዓመታትን በመንፈሳዊ ተጋድሎ በትዕግስት ሕይወት አሳልፈው ጽናትንና ብርታትን አግኝተው ነው።

ስለዚህ በእምነት በምግባር ልትመስላቸው ስትሞክር በቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አመራር ሥር ሆነህና ጥበብ የተመላበት አካሄድህን እለት በእለት እያሻሻልክ ይሁን። ሁላችን ልናገኛቸው የሚቻለን መንፈሳዊ ሥነ ምግባራትም አሉ። ለምሳሌ ትሕትና፣ ቅንነት፣ ራስን መግዛት፣ ሌሎችን መርዳት፣ መታገስ፣ ከቁጣ መራቅና የመሳሰሉትን ማዳበር እንችላለን። (ገላ 5:22)። ፍጹም ዝምታ የሚስማማህና የሚመችህ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን ከዝምታህ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ብቻ መናገርን፣ ገንቢና ጠቃሚ የሆኑ ቃላትን ብቻ መርጦ መጠቀምን ትማራለህ።

ከአቅምህ በላይ የሆነውንና ለአንተ ደረጃ የማይስማማውን በጎ ነገር ቢሆንም እንኳ ለመምሠል አትሞክር። ይህ ማለት ሙሉ ለሙሉ አይቻለኝም ብለህ ወይንም ተስፋ ቆርጠህ ተወው ማለት



www.ethiopianorthodox.org

አይደለም:: ነገር ግን የሚመራህ ባለበት የምትችለውን ደረጃ በደረጃ በማሻሻል ይዘህ እደግ ማለት ነው:: (2 ጴጥ 3:18)::

በጎ ምግባራትን ውስጣዊና መንፈሳዊ የሆነ ዋጋቸውን እንጂ ለይስሙላ ወይም ለታይታ በሚሆን መልኩ ብቻ አትውሰዳቸው:: ለምሳሌ በንስሐ የተመለሱ አባቶችን ታሪክ ስታነብ ልክ እንደእነርሱ ዳግም ወደኃጢአት የማትመለስበት ፍጹም ከልብ የመነጨ ንስሐ ለመግባት ወስን! በጸጸት የተሰበረ ልብና በእንባ የረጠቡ ዐይኖች እንዲኖሩህ አባቶችህን ምሳሌ አድርግ:: ገድላቸውንም ስታነብ ቃል በቃል ብቻ የሚሠጥህን ስሜት ብቻ ይዘህ እነሙሴ ጸሊም፣ አውግስጢኖስ እንዳደረጉት ለንስሐ የግድ ገዳማዊ መሆን እ ..ለብህ አስብህ አታፈግፍግ:: በደረጃህ ጀምር:: ንስሓ የሚገባ ሰው ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር፣ እንዴት መመለስ መቻሉን፣ ጸጸቱን፣ ኃጢአት መጥላቱን እንደምሳሌ ውሰድ:: ነገር ግን በመጠንህ በችሎታህ በተሰጠህ ጸጋ መኖርን አትርሳ::

## 2. እምነት ማጠንከር

ጠንካራ እምነት ሊመጣ የሚችለው የእምነት ጀግኖች አባቶቻችን የሠሩትን አብነት በማድረግ ነው:: እስከሞት ድረስ ለሃይማኖት የታመኑ ሲሆኑ፣ በጾም በጸሎት ተወስነው ሲኖሩ፣ የሚደርስባቸውን መከራ ሁሉ በትዕግስትና በደስታ ሲቀበሉ፣ ስናነብ የምናገኘው እጅግ ብዙ ነው:: ባላቸው ኃይልና ዕውቀት ሁሉ ቤተክርስቲያንን ጠብቀዋል:: በዚህ ምክንያት ለሚመጣባቸውም ምንም ዓይነት መከራ ጽኑዎች ሆነው በግዞት በእሥር ቤት ፈጣሪያቸውን እያመሠገኑ ኖረዋል:: ቤት አልባ ሆነው ማረፊያ እንዳጡ በስደት በየሀገሩ ተንከራተዋል:: ለምሳሌ ቅዱስ አትናቴዎስን ብንመለከት አራት ጊዜ ከፓትርያርክነት መንበሩ ተሰዷል:: በጣም አስፈሪ የነበሩ ክሶችን ሲከሰስ፣ ሲፈረድበት ብሎም «አትናቴዎስ አንተን ዓለም ሁሉ ጠልቶሃል» ሲሉት «እኔም ዓለምን ጠልቼዋለሁ» ብሎ ነበር የመለሰላቸው::

ስለዚህ ቅዱሳንን የናቀ ያ ትውልድም ሆነ የዛሬው የተነቀፈ መሆኑን እንረዳለን:: ምክንያቱም ይህ ሁሉ መሥዋዕትነት



የተከፈለበት ሃይማኖቱን የሚመለከተው በግድ የለሽነት ነው:: ያለፈውን ተጋድሎ ረስቶ ስለእምነት ወይም ስለሃይማኖት ልዩነቶች ምንም ማሰብና መጨነቅ አይፈልግም:: በአባቶቻችን ዘመን ለእያንዳንዷ የሃይማኖት ነጥብ ብሔራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ጉባኤያት ይጠሩ ነበር:: በዚህም ላይ ቅዱሳን ሃይማኖታቸው እንዲጠበቅ፣ ትክክለኛው መሠረታዊ ትምህርት እንዲታወቅ ድንቅ የሆነ ሚና ተጫውተዋል:: የሚያገኙት ግላዊ ጥቅም ሳይኖር፣ በግል የሚጎዱበትም ነገር ሳይኖር ምንቸገረኝ ያሉበት አንድም ጊዜ የለም:: ክርስትና ፍቅር ነውና ቅዱሳንም በፍቅር ውስጥ ስላሉ ሁሉ ነገር ያሳስባቸዋል:: የሌላው ጭንቀት ጭንቀታቸው ችግሩ ችግራቸው ሆኖ ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ሲሉ ሕይወታቸውን ለመስዋዕትነት አቅርበው ያለአረፍትና ያለመሰልቸት ሠርተዋል::

ዛሬ ግን በጋብቻ ወይም በፍቺ ሃይማኖት በቀላሉ ይቀየራል:: በግድየለሽነት ወይም ባለማወቅ ከቤተክርስቲያን አገልጋዮችና አባላት ባለመስማማት ብቻ ቤተክርስቲያንና ትምህርቷን ጥሎ የሚወጣው እጅግ ብዙ ነው:: ቅዱሳን ለሃይማኖታቸው ምን ያህል እንደተጋደሉ ለእርሱ ግድ አይሰጠውም:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ! በነፍስህ ጽናትንና እምነትን ለመትከል እና የማይናወጥ የማይከፋፈል ክርስቲያን ለመሆን የቅዱሳንን ሕይወት የሚናገሩትን ቅዱሳት መጻሕፍት ማንበብ ያስፈልግሃል::

ቤተ ክርስቲያን በእውነተኛ ሃይማኖት ጥላ ሥር የተሰበሰቡና ትክክለኛውን ትምህርቷን የሚከተሉ ሰዎች ማህበር እንጂ የወገን ወይንም የወገናዊነት መሰባሰቢያ አይደለችም:: በየዘመናቱ ቅዱሳን ሰማዕታት የተሠቃዩበት፣የተገረፉበት፣ የተሠየፉበት ምክንያት ሃይማኖት እንጂ ሌላ እንዳልነበረ አስተውል:: ይህን ደግሞ በየገድሎቻቸው ተጽፎ ምስክር ሆኖ እናገኘዋለን::



www.ethiopianorthodox.org

## 3. የትሕትናና የተሠብረ መንፈስን [illegible]ሰጣችን መትከል።

ቅዱሳን የነበሩበትን ፍጹም መንፈሳዊ ደረጃ ከየገድሉ[illegible] ላይ በምናነብበት ጊዜ የሚሰማን ስሜት ትሕትና እና ከእነርሱ አንጻር እኛ ምንም እንዳልሆንን ነው።

ለምሳሌ የጻድቁ አባት የአባ አብራምን ሕይወትና የለጋስነት ጸጋውን ስታነብ ልብህ አልተሠበረም? አባ አብራም ለራሱ ምንም ሳይስቀር ያለውን ሁሉ የሰጠ የመጸወተ ቸር አባት ነው። ከዚህም በላይ ሰው ለእርሱ የሠጠውን ሁሉ መልሶ ለድሆች የሚሠጥ ነበር። ያለውን ሁሉ ሽጦ ለነዳያን የሰጠውን አባ ዮሐንስን ስታስብ ምን ትላለህ? ንብረቱ ሀብቱ ቢያልቅበት እንኳን ራሱን እንደባሪያ ሽጦ ዋጋውን ለድሆች የሰጠ ሰው ይህ ቸሩ አባ ዮሐንስ (ዮሐንስ ሐር) ነው። ታዲያ እነዚህን የእግዚአብሔር ሰዎች ታ. .ፎውን እያነበብክ ስታስባቸው ራስህን እንዴት ትመለከታለህ? ገና ብዙ እድገት እንደሚቀርህና እዚያ ለመድረስ የምትድህ ከሆነ ትሕትና በውስጥህ የሚያድግበትን መንገድ አገኘህ ማለት ነው።

ጠላትህ ዲያብሎስ ራስን ከፍ ከፍ በማድረግና በትዕቢት ቢፈትንህ እንኳን የቅዱሳንን ሕይወት ስታውቅ ድካምህ ከነፍስህ ይወገዳል። አንዳንዴ የራስህ ሀሳብ አገልግሎትህን ትልቅ አድርጎ በማሳየትና ከማንም በላይ ከደከመው ከቅዱስ ጳውሎስ አገልግሎት ጋር በማነጻጸር ይዋጋሃል። (1 ቆሮ 15:10)። ይሁን እንጂ ቅዱስ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም፣ በአንጾኪያ፣ በታናሽ እስያ፣ በግሪክ እና ሮም እንደሰበከ እንዲሁም እስከ ስፔይን እንደደረሰ፣ ሊቆጠሩ የማይችሉ አብያተ ክርስቲያናትን በአንድ መሠረት ላይ እንደመሠረተ፣ በቃላት ሊገለጹ የማይችሉ ስቃይ መከራዎችን እንዳለፈ (2 ቆሮ 11) በእስር ቤት እንኳ ሳለ መልእክታትን ይጽፍ እንደነበረ፣ (ኤፌ 4:1) ስታነብና ስታስብ ውስጥህ በጸጸት አይኮማተርም? እነዚህን በመሳሰሉ ነገሮች ሁሉ ገድለ ቅዱሳን የትሕትና ምንጭ ይሆናል።

አሁን ባለህበት ደረጃ ምንም ያህል ትሑት ብትሆን ከቅዱሳን የፍጹምነት ደረጃ ጋር የምትነጻጸር አትሆንም። እነርሱ ይህን ሁሉ የቅድስና ሕይወት ይዘው በዚህ ሳይመኩ ዘወትር



ስለኃጢአታቸው የሚያለቅሱ ናቸውና። ቅዱስ አርሳንዮስ ፀሐይ ለመጥለቅ ስታዘቀዝቅ ጀርባውን ሰጥቷት ወደምስራቅ ዞሮ ለጸሎት ይቆማል። ጸሎቱን ሳያቋርጥ እንደገና ፀሐይ ከፊት ለፊቱ እስክምትወጣ ድረስ ይጸልያል። ገድሉ እንደሚነግረን በእንባ ብዛት ቅንድቦቹ የረገፉና፣ ሽፋሽፍቶቹ የተላላጡ ነበረ።

ከእንባው ብዛት ቆሞ የሚጸልይበትን የዘንባባ ዛፍ ያረጥበው ነበር። እና የቱን ያህል ትሕትና ቢኖርህ ነው ከእነዚህ አባቶች ጋር የምትነጻጸረው።

የአስቄጥስን ገዳም የመሠረተው ቅዱስ አባ መቃርዮስ በሌላ ገዳም ውስጥ ይኖሩ የነበሩትን ሁለት አባቶች ባየ ጊዜ «እኔ መነኩሴ አይደለሁም፣ ግን እውነተኛ መነኮሳትን አየሁ» ነበር ያለው። እንግዲህ ራስህን ከሌሎች እያነጻጸርክ የተሻልክና የተከበርክ አድርገህ በመቁጠር በራስህ መፈተንህን አቁም! ምክንያቱም ቅዱሳንና የሃይማኖት ተጋድሎአቸውን ብታውቅ የምትናገረው አይኖርህም። አሁን የምትረዳው ነገር ቢኖር በቤተ ክርስቲያን ጥላ ስር ማደግ እንዳለብህና ክርስቶ[illegible] የመሰሉትን ቅዱሳን በእውነት [illegible] እንዳለብህ ነው። «[illegible]እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል» (ሐዋ 14:21)።

## 4. ጥበብና ማስተዋል

ከቅዱሳን ሕይወት ተምረን የምናተርፈው 4ኛው ነገር የጥበብና የማስተዋል መንፈስን ነው። መከተል ያለብንንም ትክክለኛ መንገድ ያሳየናል። መጽሐፍ ቅዱስ ዳዊት የመሠዊያ ቦታ ለመግዛት በፈለገ ጊዜ የተናገረውን ጥበብ የተመላበት አነጋገር ያስነብበሃል። ኢያቡሳዊው ኦርናን ሁሉን ነገር ለዳዊት በነፃ ሊሠጠው ተስማምቶ ነበር። ይሁን እንጂ ዳዊት በጥበብ «እንዲህ አይደለም፣ ነገር ግን በዋጋ ከአንተ እገዛለሁ። ለአምላኬም ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መስዋዕት ያለዋጋ አላቀርብም።» (2 ሳሙ 24:24) ብሎ እንደመለሠለት እናያለን። ሌላኛው ጥበብን የሚያስተምርህ አቢግያን ዳዊትን ከቁጣ ለመመለስና ለማስማማት የተጠቀመችበት ጥበብ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

(1 ሳሙ 25:23-35)።

በወጣትነት ዘመናቸው በየበረሃው፣ በየሜካው ይንከራተቱ የነበሩ የእነ ዮሐንስ ሐጺር፣ የእንታድሮስ የቅድስና ሕይወትም ብዙ ጥበቦችን ሊያስተምርህ ይችላል። ከአረጋውያኑም አባ አጋቶን፣ አባ ኢስድሮን የመሳሰሉትን ብትመለከት ብዙ መማር ትችላለህ።

የአባቶቻችን መንፈሳዊ ጥበብ ሊማርበት ለሚወድ ተዝቆ የማያልቅ ሀብት ነው።

5. የማያቋርጥ መንፈሳዊ እድገት

ከገድለ ቅዱሳን የምናገኘው ሌላው ጠቃሚ ነገር የማያቋርጥ መንፈሳዊ እድገት ነው። ምንም የሚገታው የሌለ፣ ሥጋን የሚገሉ የክርስትና ጠላቶች የማይገድሉት፣ መንፈሳዊ እድገታቸው ሁሌ ወደላይ የሚያድግ ነው። ከሥጦታው ሁሉ ጋር የቅዱስ ጳውሎስ አገልግሎት እንዲሁም እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ የመነጠቅ ብቃቱ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። እርሱ ግን እንዲህ ነበር ያለው።

«አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደሆንኩ አይደለም። ነገር ግን ስለእርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ። ወንድሞቼ ሆይ ገና እንዳልያዝኩት እቆጥራለሁ። ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ። በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ። በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ።» (ፊልጵ 3:12)።

ቅዱሳን በደግነት፣ በጥሩ ምግባር የደረሱበት ከፍተኛ የመንፈሳዊ እድገት ደረጃ አንተን ዛሬ ባለህበት እንዳትታበይ፣ ለሚበልጠው እንድትጥርና እድገትህ እንዲቀጥል የሚያደርግ ነው። በፊትህ ያለው መንገድ ረጅም ነው። ነገር ግን የሚሠጥህን ጸጋ በእጅህ ልትቀበለው የቀረበ በመሆኑ ቅዱሳንን እግር በእግር እየተከተልክ በመከራ፣ በፈተና ውስጥ እንኳ ቢሆን በቁርጠኝነት ማለፍ እንድትችል ያበረታሃል።



የቅዱሳን ሕይወት የማይጠፋና ሊጨቁኑት የማይቻል የጋለ መንፈሳዊ ስሜትን የሚሰጥ ነው።

ከእነዚህ በተጨማሪ ገድለ ቅዱሳን በሌሎችም በተለያዩ መንገዶች በአንተ ላይ አዎንታዊ ተጽእኖዎችን ማሳደር ይችላል።

የንስሐ ሕይወትህ ፍጹምና ትክክል እንዲሆንና፣ በውስጥህም ያለውን ጉድለት በጽድቅ ፍሬዎች ለመሙላት ምን ማድረግ እንዳለብህ ከቅዱሳን ትማራለህ።

በፍጹም ወዳጅነት፣ በትሕትናና፣ በፍቅር ይጸልዩት የነበረውን ጸሎታቸውን ከገድላቸው ስታነብ እንዴት መጸለይ እንዳለብህ ታውቃለህ ።

ሰዎች በመንፈሳዊ ጦርነት በነበሩበት ጊዜና ድል አድራጊዎች በሆኑበት ጊዜ እንዴት አብረህ መኖር እንደምትችል፣ ችግረኞችን እንዴት መንከባከብ እንዳለብህ ታይበታለህ።

የቅዱሳንን ሕይወት በመጽሐፋቸው ውስጥ ስትመለከት፣ በአነጋገርህ፣ ስለሰዎች ባለህ አስተሳሰብና፣ በአጠቃላይ በነገር ሁሉ የማያቋርጥ መሻሻል እያደረግህ ነው።

እባክህ ይህን ልምድ በውስጥህ እንዲያድግ ፍቀድለት? እስከአሁን ያልኩህ ሁሉ የምሳሌ ያህል እንጂ ምሉዕ የሆነ ነገረ ቅዱሳን እንዲህ በቀላሉ የሚደፈር አይደለም። ራሱን ችሎ እንኳን ቢቀርብ መጽሐፍ እሊያም መጻሕፍት የሚያስፈልገው ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ውድ ወንድሜ ሆይ፡- የቅዱሳንን ሕይወት እንድትመቀምበት ይህን ሠፊ የተመሰጠ ውቅያኖስ ለአንተ መተውን መርጫለሁ። ምክንያቱም ይህ ጉዳይ ማናቸውንም የመንፈሳዊ ሕይወት እንቅስቃሴዎች የሚዳስስ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውምና ነው።

አዘጋጅ፡- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ

ተርጓሚ
ዲያቆን ግርማ ባቱ
በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ
የ3ኛ ዓመት የዲግሪ ተማሪ

www.ethiopianorthodox.org